EMBARGOED FOR RELEASE
10:30 a.m., U.S. Eastern Time
Thursday, 1 October

CONTACT: Natasha Pinol
+1-202-326-7088
npinol@aaas.org

# ከ"ሉሲ" በፊት "አርዲ" ነበረች፦ በጥንታዊነታቸው ከሚታወቁት ከመጀመሪያዎቹ የሰው ዝሪያዎች (ሆሚኒዶች) አንዱ ላይ የተደረገ የመጀመሪያ ታላቅ ትንታኔ በሳይንስ መጽሔት ልዩ እትም ላይ ወጣ

አንድ የአለም አቀፍ ሳይንቲስቶች ቡድን፤ አሁን ኢትዮጵያ ተብሎ በሚጠራው የዛሬ 4.4 ሚሊዮን ዓመት ይኖር የነበረ አርዲፒቴከስ ራሚደስ (*Ardipithecus ramidus*) ተብሎ የሚጠራ ከሆሚኒድ ዝርያዎች አንዱ ስልሆነው፤ በሳይንስ መጽሔት ልዩ እትም ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በዝርዝር አብራርቷል። ይህ በ11 ዝርዝር ጽሑፎችና ማጠቃለያዎች የቀረበ ጥናት በኦክቶበር 2/2009 በሚወጣው እትም ላይ ይቀርባል። ሳይንስ መጽሔት የሚታተመው AAAS በሚባለው ያለትርፍ በሚንቀሳቀስው የሳይንስ ማህበረሰብ ነው።

ይህ የምርምር ጥናት ስብስብ በሌሎች ተመራማሪዎች ግምገማ የተደረገበት፣ የአርዲፒቴከስ (*Ardipithecus*) ቅሪት አካሎች፣ በቅጽል ስም "አርዲ" ተብላ የምትታወቅ ከፊል የሴት አጽምን ጨምሮ የመጀመሪያ ጥልቅ ገለጻ ያቀርባል።

ሰዎችና ቺምፓንዚዎች ይጋሩት የነበረው የመጨረሻው ቅድመ አያት የዛሬ ስድስት ሚሊዮን ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ይኖር ነበር ተብሎ ይታመናል። አርዲፒቴከስ (*Ardipithecus*) እራሱ ይህ የመጨረሻው የጋራ ቅድመ አያት ባይሆንም፣ ከዚህ ቅድመ አያት ባህርዮች ብዙዎቹን የያዘ ነበር ተብሎ ይታሰባል። በንጽጽር አርዲፒቴከስ (*Ardipithecus*) የ"ሉሲ" ዘር የሆነውን ኦስትራሎፒቴከስ አፋረንሲስን (*Australopithecus afarensis*) ከፊል የሴት አጽም ቢያንስ በአንድ ሚሊዮን ዓመት የበልጠዋል። አዲሱ የአርዲፒቴከስ (*Ardipithecus*) ቅሪት እስከሚገኝ ድረስ፤ የሌሎች ቅሪት አካሎች መዝገብ ከኦስትራሎፒቴከስ (*Australopithecus*) በእድሜ የሚበልጡ ሌሎች ሆሚኒዶች እንደነበሩ እምብዛም መረጃ አያሳዩም ነበር።

የራስ ቅል፣ ጥርስ፣ የዳሌ፣ የእጆች፣ የእግሮችና ሌሎች አጥንቶችን ካጠኑ በኋላ ተመራማሪዎቹ አርዲፒቴከስ (*Ardipithecus*) ቀደም ብሎ Miocene epoch (በማዮሲን ዘመን) በቦታው ከነበሩት ጋር ተመሳሳይ የሆነ የ"ጥንታዊ" ባሕርዮች የነበሩትና እንዲሁም ቀጥሎ ከመጡት ሆሚኒዶች "የተወረሱ" ባሕርዮች ሙሉ በሙሉ እንደሚጋራ ለመገምገም ችለዋል።

ጥንታዊነቱ የላቀ ስለሆነ፣ አርዲፒቴከስ (*Ardipithecus*) አሁንም አልጨበጥ ያለው የጋራ ቅድመ አያት ጋር ለመድረስ ቀረብ እንድንል ያደርገናል። ሆኖም ብዙ ባሕርዮቹ ዘመናዊ የአፍሪካ ዝንጀሮዎች ላይ አይታዩም። በሚገርም ሁኔታ፣ ይህ የሚያሳየው የአፍሪካ ዝንጀሮዎች የመጨረሻ ቅድመ አያት በጋራ ከነበረን ጊዜ ወዲህ በሰፊው እንዳደጉና ይህም በሕይወት ያሉ ቺምፓንዚዎችና ዝንጀሮዎች የመጨረሻው

የጋራ ቅድመ አያት ለመሆን ጥሩ ምሳሌ እንዳልሆኑና ከዛን ጊዜ ጀምሮ የራሳችንን እድገት/ለውጥ ለመረዳት እንደማያስችሉ ነው።

"*አርዲፒቴከስ* (*Ardipithecus*) ወደ *አስትራሎፒቴከስ* (*Australopithecus*) አቅጣጫ ብዙም ያላደገ ያልለየለት ፍጥረት ነው። ከጭንቅላቱ እስከ እግር ጣቶቹ ሲታይ ቺምፓንዚም ያልሆነ ሰውም ያልሆነ ቅልቅል ፍጥረት የሚታይብት፣ *አርዲፒቴከስ* (*Ardipithecus*) ነው፤" ሲሉ በበርክሊ ካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ የሚገኙት ከጥናቱ ዋና ጸሓፊዎች አንዱ የሆኑት Tim White ተናግረዋል።

"አጽሙ የተሟላ በመሆኑና በዛ ጊዜ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ሌሎች ተመሳሳይ ዘር የሆኑ ብዙ ስላሉ የዚህን የመጀመሪያው የሰው ዘር ስነ ህይወት በደንብ መረዳት እንችላለን፤" ሲሉ የቶኪዮ ዩኒቨርሲቲ ፕሮጀክት ፓሌዮንትሮፖሎጂስት እና የ*ሳይንስ* መጽሔት ዋና ጸሐፊ የሆኑት Gen Suwa ተናግረዋል።

"እነዚህ ጽሑፎች በዋና የአለም አቀፍ ጥናት ጥረት የተደረገበት በጣም ብዛት ያላቸው የተሰባሰቡና ትንታኔ የተደረገባቸው መረጃዎችን የያዙ ናቸው። ስለ ሰው አዝጋሚ እድገት ላለን ጥቂት እውቀት የመጀመሪያዎቹ የሰው ዘሮች ከአፍሪካ ዝንጀሮዎች ጋር በመጨረሻ የጋራ ቅድመ አያት የነበራቸውን ለቀው ለብቻቸው እንደተለዩ እራሳቸውን በአፍሪካ ውስጥ ሲያቋቁሙ የነበረበት ዘመን ውስጥ እይታ እንዲኖረን በር ይከፍታሉ፤" ሲሉ የ*ሳይንስ* መጽሔት ፊዚካል ሳይንስ ምክትል አዘጋጅ Brooks Hanson ተናግረዋል።

"*ሳይንስ* መጽሔት ይህንን የመጀመሪያው የሰው ዘር አዝጋሚ እድገት ዋና መሠረቱ ላይ አዲስ አስተያየቶች የሚሰጥ እና የሰው ልጅን ከፕራይሜቶች/ሰው መሰል ፍጥረቶች ልዩ የሚያደርገው ምን እንደሆነ የሚያሳይ አዲስ መረጃ በማተሙ ደስታ ይሰማዋል፤" ሲሉ Hanson ገልጸዋል።

የ*ሳይንስ* መጽሔት ጽሑፎች ልዩ ስብስብ የሚጀምረው የጥናቱን ዋና ግኝቶች በአጭሩ በሚገልጽ ጽሑፍ ነው። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ፣ White እና ተባባሪ ጸሐፊዎቹ፣ አብዛኛው የራስ ቅል፣ እጆች፣ እግሮች፣ ሌሎች የአካል ክፍሎችና የዳሌ አጥንቶች ያለው ከፊል አጽምን ጨምሮ ከ110 በላይ *አርዲፒቴከስ* (*Ardipithecus*) ናሙና ግኝቶቻቸውን ያስተዋውቃሉ። ይህች "አርዲ" ተብላ የምትታወቅ ግለሰብ፣ 50 ኪሎግራም የምትመዝንና 120 ሴንቲሜትር ርዝመት ያላት ሴት ነበረች።

እስካሁን ድረስ ተመራማሪዎች ቺምፓንዚዎች፣ ዝንጀሮዎችና ሌሎች ዘመናዊ የአፍሪካ ዝንጀሮዎች በመጨረሻ ከሰው ልጅ ጋር በጋራ ከነበራቸው ቅድመ አያት ጋር ተመሳሳይ ባህርዮች ጠብቀው ቆይተዋል ብለው ያምኑ ነበር፣ በሌላ አነጋገር ይህ ቅድመ አያት ከሰው ይልቅ ከቺምፓንዚ ጋር ይበልጥ ተመሳሳይነት አለው ተብሎ ይታሰብ ነበር። ለምሳሌ ከዛፍ ቅርንጫፎች መንጠላጠልና መወዛወዝ የለመደና መሬት ላይ ሲሆን ደግሞ በእጅና በእግር ጣቶቹ የሚራመድ ነበር።

ነገር ግን *አርዲፒቴከስ* (*Ardipithecus*) እነዚህን አስተሳሰቦች አጠራጣሪ ያደርጋል። እነዚህ የመጀመሪያዎቹ የሰው ዘሮች በእንጨት ባለበት አካባቢ ይኖሩ እንደነበር

ያመለክታሉ፣ ዛፎች ላይም ሲወጡ እንደ አንዳንድ ማዮሲን ፕራይሜቶች እጃቸውንም እግራቸውንም ተጠቅመው ሲሆን፣ መሬት ላይ ሲሆኑ ደግሞ ቀጥ ብለው በሁለት እግራቸው የሚራመዱ ነበሩ። በተለይ ቺምፓንዚዎች እንደሚያደርጉት በእጅ ጣታቸው የሚራመዱ አይመስሉም፤ ወይም ከዛፍ ቅርንጫፎች ብዙም የሚንጠላጠሉ ወይም የሚወዛወዙ የነበሩ አይመስሉም። ባጠቃላይ ግኝቶቹ የሚያሳዩት የመጀመሪያዎቹ የሰው ዘሮች እና የአፍሪካ ዝንጀሮዎች የተለያየ የእድገት መንገድ እንደተከተሉና ቺምፓንዚዎችን በመጨረሻ በጋራ ለነበረን ቅድመ አያት ''መሰሎች'' ናቸው ብለን መውሰድ እንደማንችል ነው።

" Darwin በዚህ ጉዳይ ላይ በጣም አስተዋይ ነበር፣" ብለዋል White ።

" Darwin በጣም መጠንቀቅ አለብን ብለዋል። ይህ በመጨረሻ የነበረው የጋራ ቅድመ አያት ምን ይመስል እንደነበረ የምናውቀው ወደዛው ሄደን በማግኘት ብቻ ነው ብለዋል። እንግዲህ እርሱን በቅርብ ሊመስለው የሚችል ነገር ያገኘነው የዛሬ 4.4 ሚሊዮን የነበረውን ነው። ልክ Darwin እንደሚያደንቁት፤ በመጨረሻ የጋራ ቅድመ አያት ከነበረን በኋላና ያ ዝርያ ከተከፈለ በኋላ፣ የዝንጀሮ ዝርያ እድገትና የሰው ልጅ ዝርያ እድገት ለየብቻቸው ሲካሄዱ ቆይተዋል፣" ሲሉ White ተናግረዋል።

ይህ *የሳይንስ* ልዩ እትም አንድ አጭር መግለጫ፣ *አርዲፒቴከስ* (*Ardipithecus*) ይኖርበት የነበረውን አካባቢ የሚገልጹ ሶስት ጽሑፎች፣ አምስት *የአርዲፒቴከሶን* (*Ardipithecus*) የሰውነት ክፍሎች የሚተነትኑ ጽሑፎች እና ሁለት ይህ አዲስ ሳይንሳዊ መረጃ ለሰው እድገት ምን ዓይነት አስተዋጾ እንደሚያቀርቡ የሚናገሩ ጽሑፎችን ይዟል።

ባጠቃላይ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ አርባ ሰባት የተለያዩ ጸሐፊዎች ለዚህ *የአርዲፒቴከስ* (*Ardipithecus*) እና አካባቢው ጥናት አስተዋጾ አድርገዋል። ዋና ጸሐፊዎቹ Tim White ከበርክሊ የካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ፣ Berhane Asfaw የስምጥ ሸለቆ ጥናት አገልግሎት በአዲስ አበባ፣ Giday WoldeGabriel ከሎስ አላሞስ ብሔራዊ ላቦራቶሪ፣ Gen Suwa ከቶኪዮ ዩኒቨርሲቲ እና C. Owen Lovejoy ከኬንት ስቴት ዩኒቨርሲቲ ናቸው።

"እነዚህ ጥልቅ ወደሆነው አፍሪካዊ ታሪካችን ተጉዘን ያገኘናቸው ውጤቶች ናቸው፤" ብለዋል የፕሮጄክት ተባባሪ-ዳይሬክተር እና ጂኦሎጂስት የሆኑት WoldeGabriel።

***

ሥራ ላይ ያሉ ጋዜጠኞች *የሳይንስ* መጽሔት ድረ-ገጽን በwww.eurekalert.org/jrnls/sci አድራሻ በመጎብኘት፣ የሕትመት ስብስብ ቡድኑን በስልክ ቁጥር +1-202-326-6440 በመገናኘት ወይም በኢሜል scipak@aaas.org በመጻፍ የ11ዱንም ረቂቶች ግልባጭና ተዛማጅ አንድ ገጽ ርዝመት ያላቸውን ጸሐፊዎቹ የጻፉትን አጭር ጽሑፎች ማግኘት ይችላሉ። 11ዱም ጽሑፎች በቀላሉ በሚገባ ቋንቋ ባጭሩ ተጽፈው፣ እንዲሁም ተዛማጅ ስእሎችና ከ Dr. White ጋር

የተደረገ ቃለምልልስ በድምጽ ተቀርጾ፣ እናም ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችም እዚሁ ድረ-ገጽ ላይ ይገኛሉ።

በሳይንስ መጽሔት ጽሑፎች ላይ የተደረገው ማእቀብ ሐሙስ ከጠዋቱ 10:30 ET ላይ ይነሳል፤ ይህም ሰዓት ዋሽንግተን ዲሲ AAAS እና አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ መግለጫ የሚሰጥበት ሰዓት ይሆናል። እነዚህ ዝግጅቶች በሳተላይት የሚቀዱ ሲሆን የ AAAS ዝግጅቱ በኢንተርኔት ላይ በቀጥታ ይተላለፋል። የAAAS ዝግጅቱ ላይ መገኘት የሚፈልጉ ጋዜጠኞች አስቀድመው በscipak@aaas.org አድራሻ ኢሜል በመላክ እንዲያሳውቁ እንጠይቃለን።  በይበልጥ መረጃ ለማግኘት እባክዎን የሳይንስ መጽሔት የሕትመት ስብስብ ድረ-ገጽን ይጎብኙ ወይም የሳይንስ መጽሔት ሕትመት ቡድን ያነጋግሩ።

ይህ ጥናት የገንዘብ ድጋፍ ያገኘው ከብሔራዊ የሳይንስ ድርጅት፣ በሎስ አላሞስ ናሽናል ላቦራቶሪ (LANL) ከሚገኘው የካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ የጂዮፊዚክስ እና የመሬትና አካባቢ ፊዚክስ ተቋም፣ የጃፓን ማህበረሰብ የሳይንስ ድጋፍ እና ከሌሎችም ነው።

የ American Association for the Advancement of Science (AAAS) ከዓለም ትልቁ አጠቃላይ የሳይንስ ማህበረሰብ እና የሳይንስ መጽሔት አታሚ ነው (www.sciencemag.org)።  AAAS በ1848 ዓ.ም. የተቋቋመ ሲሆን፣ ለ10ሚሊዮን ግለሰቦች አገልግሎት የሚሰጡ 262 ተባባሪ ማህበሮችን እና የሳይንስ ማስተማሪያ ተቋማትን ያገለግላል።  ሳይንስ መጽሔት ከማንኛውም በክፍያ የሚገኝ በጥንቃቄ ግምገማ የተደረገበት የአጠቃላይ ሳይንስ መጽሔቶች ሁሉ በብዛት የሚሸመት ሲሆን በግምት አንድ ሚሊዮን አንባቢ አለው።  ያለትርፍ የሚሰራው AAAS (www.aaas.org) በሩ ለሁሉም የተከፈተ ሲሆን፣ ዓላማው በሳይንስ ፖሊሲዎች፣ በዓለም አቀፍ መርሃ ግብሮች፣ በሳይንስ ትምህርት እና በሌሎች መንገዶች "ሳይንስን ወደፊት ለማራመድና ማህበረሰብን ለማገልገል" ነው።  በቅርብ የወጡ የጥናት ዜናዎችን ለማንበብ AAAS የሚያቀርበውንና ሳይንስ-ነክ ዜናዎችን በማቅረብ አንደኛ የሆነውን EurekAlert!ን በድረ-ገጽ www.eurekalert.org ይጎብኙ።